# *በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ መኖር*

## ትምህርት ሶስት፡- የመንግስቱን መርሆዎች ማውቅ

**ዓላማ**፡-

-በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ለመኖር የመንግስቱን መርህ የማወቅ አስፈላጊነትን ማሳሰብ።

- የመንግስቱን መርህ ምንነት ማውቅ ተግቢውን የህይወት ስርዓት ለመምራት እንደሚያስችል ማመላከት።

-አማኞች እንደ እግዚአብሔር መንግስት ዜጋ እንዲኖሩ ማበረታታት።

**መግቢያ**፡-የእግዚአብሔርን መንግሥት መርሆች ማወቅ ለእያንዳንዱ አማኝ በጣም አስፈላጊ ነው። **ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር በሚስማማ መንገድ እንድናስብ ፣ እንድንኖር፣ እና እንድናገለግል ህይወታችንን ስለሚቀርጽው**።ከዚህ እውነት አንጻር የመንግስቱን መርህ ማውቅ አስፈላጊ የሆነበትን መጸህፍ ቅዱሳዊ ቁልፍ ምክንያቶችን በዚህ ትምህርት እንመለከታልን።

## 1. የእግዚአብሔርን ፈቃድ እና መንገዶች መረዳት

እንደ **ጽድቅ፣ ፍትህ፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ እምነት እና ታዛዥነት** ያሉ የእግዚአብሔር መንግስት መርሆዎች **የእግዚአብሔርን ተፈጥሮ እና ከህዝቡ የሚጠብቀውን መላሽ ይገልጣሉ።** እነዚህን ማወቃችን **ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር እንድንራመድ ይረዳናል** (ሮሜ 12፡2)።

## 2. የመንግሥቱ ዜጎች ሆነን ለመኖር

ጌታችን ኢየሱስ **“የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለች”** (ማር. 1፡15)ብሎናል ። ይህ ማለት መንግሥተ ሰማይን እየጠበቅን ብቻ አይደለም ማለት **ነው።ስለሆንም የተጠራነው**

**እንደ መንግሥት ዜጎች እንድንኖር ነው**። መርሆቹን መረዳታችን ደግሞ **በምድር ላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድንወክል ይረዳናል** (ፊልጵስዩስ 3፡20)።

## 3. መንፈሳዊ እድገት እና ብስለትን ያስገኝልናል።

**የመንግሥቱን መሠረታዊ መርህ ማወቅ ወደ መንፈሳዊ እድገት ይመራናል።** ኢየሱስ በማቴዎስ 6፡33 ላይ **"አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ..."ብሎናል**። ይህ ማለት **ወደ ጥልቅ እምነት፣ በተልወጠ ባህርይ እና በአላማችን ላይ ትኩረት ማድረግ ነው።**

## 4. ውጤታማ አገልግሎት እና ምስክርነት እንዲኖረ ያደርጋል

**ወንጌልን ለማካፈልና በብቃት ለማገልገል** በመጀመሪያ **የምንወክለውን መንግሥት ማለትም እውነትን፣ ምሕረትን፣ አገልግሎትንና ቅድስናን ማወቅ አለብን**። ይህ **ለምስክርነታችን ትክክለኛነትን ያመጣል** (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡20)።

## 5. በዓለም ስርዓቶች ላይ ድልን ያስገኝልናል።

**የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሠራው ከዓለም በተለየ ሁኔታ በትሕትና፣ በፍቅር እና በይቅርታ ነው። እነዚህን መርሆች መረዳታችን ዓለምን ለማሸነፍ ኃይል ይሰጠናል** (ዮሐንስ 18፡36፤ 1 ዮሐንስ 5፡4)።

**ማጠቃለያ**፡-በአጠቃላይ የእግዚአብሔርን መንግሥት መርሆች ማወቅ አማኞች **በዓላማ እንዲኖሩ**፣ **ክርስቶስን በታማኝነት እንዲያንጸባርቁ** ፣ **ከስህተት ትምህርትና አሰራር እዲያመልጡ** እና **ለሚመጣው ንግሥና/የእግዚአብሔር መንግስት ፍጻሜ እንዲዘጋጁ ኃይል ይሰጣቸዋል።** ስለዚህ የመንግስቱ መርህ ማወቅ ለአማኝ ወሳኝ ነው የምንለ ለዚህ ነው።ስለዚህ የመንግስቱን መርህ እንወቅ።